## *ያድናል የተባለ ኩሉ ዓይን እንዳያጠፉ!!*

***ኃይሌ መለሰ (ብ/ጀኔራል)***

ሞት አይለመድም እንጅ ለሁሉም የሰው ልጅ ከፈጣሪው ያለአድልዎ የታደለው የተፈጥሮ ሐብቱ በመሆኑ እንግዳ ነገር አይደለም እየተባለ በአበው ሲነገር እሰማ ነበር፣ ነውም። አገር በማጥፋት በከበሩትና ችግር በመፍጠር በተካኑት በወያኔዎችም ዘመን እንደሞት ያልለመድነው፣ ግን በየወሩና በየዓመቱ ብቻም ሳይሆን በየዕለቱ ማለትም ይቻላል ኅሊናን የሚያቆስልና አንጀትን አሳርሮ የሚያኮማትር ቀጣይ ችግር አሳጥተውን አያውቁም።

እኛም ካለፈው የማንማር ማይሞች፣ ውርደትና ጥቃቱ የማይመረንና ችግሩ የማያንገፈግፈን የባህሪ ድሃዎች በመሆናችን እርስበርሳችን የምንናከስበትን ጥርስና የምንራከስበትን ምላስ ወደጋራ ጠላቶቻችን አዙረን የምንስልና የምናሾል አልሆንም። ከዚህ ይልቅ ጥፋትን ፅኑዕ ዕምነታቸውና ማጥፋትን የግብር መግለጫቸው አድርገው የዘመቱብን የዘመኑ ዮዲት ጉዶችና አህመድ ግራኞች ዘርተው ለሚያበቅሉልንና እየኮተኮቱ ለሚያሳድጉልን የመጠፋፊያ ችግር ችግኝ መትከያ ያዳበረ ማሳና ማዳበሪያ ኬሚካል ሆነን በማገልገል በራሳችን ላይ እየዋልን እነሱ እኛን ጨርሶ ለመግደል ያዘጋጁልንን መሣሪያ እየወለወልን የምናቀርብላቸው ባለውለታዎቻቸው ሆነንላቸዋል።

ሰሞኑን ደግሞ የሁለት ሺኛው ዓመት መቀበያ ሆኖ የቀረበልን ያልጠበቅነው አዲስ መርዶ እንደወርቅ በችግር እሣት ውስጥ ተፈትነው ያለፉ ጀግኖችና በቃላቸው የጸኑ ባለማተቦች ናቸው ብለን ከፈተኛ ዕምነት በጣልንባቸው የቅንጅት መሪዎች መካከል የተፈጠረው ክፍተትና ጎራ ለይቶ በመካሄድ ላይ ያለው የእርስ በርስ መቋሰያ የቃላት ጦርነት ነው። ይህ ያልተጠበቀ አሳዛኝ ድርጊት በአንድ በኩል ሰፊውን ሕዝብና በቅንጅት ዙሪያ ተሰባስቦ የራዕዩን ዕውንነት በተስፋ ሲጠባበቅ የነበረውን ወገን ሁሉ ካልጠበቀው ከባድ ሐዘን ላይ ሲጥል፣ በሌላ በኩል ደግሞ በቅንጅት ተጠናክሮ መውጣት እንከስማለን የሚል አደጋ ተጋርጦባቸው ለነበሩት የአንድነት ጠላቶችና ለእኛ ያልሆነ ሠርዶ ከሥሩ ተነቅሎ ይድረቅ ብሎ ረጋሚ ለሆኑት ዕውቅ የመልካም ሥራ ፀሮች ግን የሚያስፈነድቃቸው ሆኖ እየታየ ነው። በተለይም ወያኔዎች በምዕት ዓመቱ አከባበር ለደረሰባቸው ሁለንተናዊ ሽንፈት ያልጠበቁት ማካካሻ ስለሆነላቸው ክፍተቱን የበለጠ ለማስፋትና ተመልሶ እንዳይገጥም ለማድረግ እየተራወጡ ነው። ተበዳዮቹ የቅንጅት መሪዎች ሳይበድሉ እንደበደለኛ የተቀበሉትን የመፈቻ «ጥፋተኞች ነን» ባይነት ኅሊናየ ባይቀበለውም በመፈታታቸው ግን ከቅርብ ቤተሰቦቻቸውና ጽኑዕ የዓላማ አጋሮቻቸው ባላነሰ ምን ያህል ከፍተኛ ደስታ ተሰምቶኝ እንደነበር ከሌላው ምሥክርነት በበለጠ ይታዘበኛል ብየ በጣም የምፈራውን ኅሊናየን ዋቢ አድርጌ ብቆም ያስተባብለኝ ይሆን ብየ አልሰጋም። ያ ባሳዩን ጽኑነት ታጅቦ የነበረው ተስፋየና ማገገም ጀምሮ የነበረው የኅሊና ቁስሌ በእንደዚህ ያለው ያልተጠበቀ አሳዛኝ ድርጊት በመለወጡ ግን በእጅጉ አዝናለሁ።

እኔ የቅንጅት መሪዎችን አያቸው የነበረው አደጋ ላይ ለወደቁት ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ቁርጥኛ ታዳጊዎች፣ የሕዝብ ነፃ አውጭዎችና (የወንድማማችነትና የእህትማማችነት) ፍቅር አላባሾች፣ የብሩህ ተስፋ ራዕይ ዓላሚዎችና ተርጓሚዎች፣ ከአድማስ ባሻገር መመልከት የሚችል ብሩህ አእምሮ ያላቸው መሪዎች አድርጌ ነበር። ከሁሉም በላይ ደግሞ በሁሉም ነገር ውስጥ ያለፉና ሁሉንም ነገር ንቀው በመተው ተጥሎ በመረገጥ ላይ ያለውን ኢትዮጵያዊ ለማንሳት ሲሉ ብቻ ቆርጠው የተነሱ የሕዝብ የቁርጥ ቀን ልጆች ናቸው ብየ ነበር። እንዲያውም ጠላቶቻችን ደቅነውባቸው ለነበሩት ውስብስብ ችግሮች ያልተበገሩ ጀግኖች ራሳቸው በፈጠሩት ውስጣዊ ችግር የሚደፈርሱና ጎራ ለይተው የሚወራከቡ ሰዎች ይሆናሉ የሚል ጥርጣሬ ከቶዉንም አልነበረኝም።



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ባለመታደል ልበለውና እኛ ከራሳቸው በላይ አድርገን ስላየናቸውም ይሁን ወይም እነርሱ የተናገሩትን ያህል ሆነው ባለመገኘታቸው እንደሆነ አላውቅም የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዊነት ደመኛ ጠላቶች ለእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ቤተሰብ እንደራሺን ያደሉት ሐዘንና በየበራፉ የተከሉት የሐዘን ድንኳን ሳይነቀል በነበረበት እንዲቀጥል የሚያደርግ ተጨማሪ መርዶ እያረዱት መሆናቸው ነው:: ድርጊታቸው ያሰደረብኝን ቃላት የማላገኝለት ትዝብት ለመግለጽ ስል *«ያድናል የተባለ ኩል ዓይን እንዳያጠፋ!»* በሚል ርዕስ እንድገልፀው የተገደድኩትም በዚህ ምክንያት  ነው::

ግንባር ቀደም መሪዎቹ ተካፋፍለው እነሱ የሚመሩት ቅንጅት እንዳልተከፈለ አድርገው የሚሰጧቸውን መግለጫዎችና እየመረጡ የሚወራወሯቸውን ቃሎች በተቻለኝ መጠን ተከታትያለሁ:: መከታተል ብቻም ሳይሆን ችግሩ የት ላይ እንዳለም ያለማጉያ መነጽር ማነበብ ችያለሁ:: «**እገሌ ነው**» ብየ ለመፈረጅ ግን ትናንት መርጦ ያስቀመጣቸውንና ብዙ ችግር አይቶ ያስፈታቸውን ሕዝብ ስልጣን መጋፋት ስለሚሆንብኝ ዛሬም የእርሱን ሁለተኛ ዙር ብይን መጠበቅን መርጫለሁ:: የኾም ሆኖ አጠቃላይ ሁኔታውን በተወሰኑ ነጥቦች ላይ ተመሥርቼ ያለኝን አስተያየት ለመስጠት እሞክራለሁ::

በመሠረቱ በዎያኔዎችና በአንድነት ኃይሎች መካከል ካሉት ሰፊ ልዩነቶች አንዱ ተቀራርቦ በመወያየት ያገጠጡትን አገር አቀፍ ችግሮች ለመፍታት አለመቻል ነው:: የዓላማና የግብ ልዩነትን ሳይጨምር በሌላ አባባል ይነገርና ሌሎች ሰዎች ይናገሩት እንጅ በቅንጅት መሪዎች መካከል ሲደገም የምናይና የምንሰማው ይህንኑ የሚያመለክት ነው:: የሰማኋቸውን ለኅሊና መጣፈጥ ቀርቶ እንዲያውም ኅሊናን የሚደፈጥጡ ቃላት ሁሉ ልተርጉማቸው ብል እኔም እነዚያኑ መልሶ መድገም ስለሚሆንብኝ እንዳጠናክራቸው ኅሊናየ አልፈቀደልኝም:: ነገር ግን ኢትዮጵያን ታከል ታሪካዊት አገርና ሰባ ሚሊዮንን ያህል ሰፊ ሕዝብ የማዳን ታሪካዊ ሃላፊነትን የተሸከመ አመራር የገባው ቃል - ኪዳን ሸክሙ ከብዶት ከመጉበጥና ሃላፊነቱ ሰፍቶበት ከመጨነቅ ይልቅ ገና ምኑም ሳይያዝ የፕሮቶኮል ጥያቄ ቅድሚያ ተሰጥቶት ስለጉብኝት ፕሮግራም መቀዳደምና ስለአውሮፕላን ጣቢያ አቀባበል መወራከብ ነበረባቸው?

ለሕዝብ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብት መከበርና ለእናት ሀገር ብሔራዊ ህልውና ሲባል በግፍ የመገደል ታናሽ ወንድም የሆነው ታሥሮ መሰቃየት (ማንዴላን ያዘክሯል) ለምን ተቃልሎ እንደታየ ባይገባኝም ያ: መፈናፈኛ የሌለው መራራ የችግር ቦታ የፈተነው ዕምነትና ያስተቃቀፈው ሰውነት፣ ያ: የቀን ጨለማ ሌሊት ያጋባው ቃል - ኪዳንና የገነባው ፍቅር፣ እንደውሎ ገብ ገበያተኛ የእግር ብረቱ ከተፈታልንስ ብሎ ሁሉም በየአፈተተው የሚነጉድበት ነውን? ስለዕውነት ያ: በቁጭት የታጀበ የሕዝብ ጭንቀት፣ የእነዚያ ዉድ የእናት ሀገር ልጆች ክቡር መስዋዕትነትና ስቃይ ውጤቱ ይህ ከሆነ «የተናገሩት ከሚጠፋ የወለዱት ይጥፋ» አባብሎ ቢያረጋግም የሚያስፈርድ አይመስለኝም::

ምንም የደረግ በማን የቅንጅትን ጠንካራ መሠረት የጣለ የፖለቲካ መሐንዲስ በፕላኑ መሠረት ለግንባታው መፋጠንና ለአፈጻፀሙ ማማር ከመጣርና ከመጋር ይልቅ የከሠረ ነገር አምራች ከሆኑ ልማደኛ ነገረኞች ጋር ሆኖ መልሶ ሊንደው የሚችል የነገር ፈንጅ መቀመም ግን የሕዝብ አደራ የሚከብደው ሰው አስቦ የሚያደርገው ጤናማ ሥራ ነው ብሎ ለማመን በእጅጉ ይከብዳል::

ጻድቁ ዮሐንስ የተባሉ ንጉሥ እንደ አሁኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያልጠበቁት ፈተና ገጥሞአቸው «ከዚህ ያለነው ሦስታችንም ዕውነት ብንናገር ተጠብሶ የቀረበልን አሳ ነፍስ ዘርቶ በሄደ ነበር» እንዳሉ ታሪክ ይናገራል:: ከዚህ አንጻር የቅንጅት መሪዎችም በፖለቲካ ቋንቋ ዙሪያ እየተሽከረከሩ ከዚህ ደረጃ ላይ ያደረሳቸውንና የተላበሱትን ክብርና ሞገስ ያጎናጸፋቸውን ባለማተብ ሕዝብ ከሚያስጨንቁትና ከሚያደናግሩት ይልቅ ቅንጅት በቅንጅትነቱ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ሊያደርግ የሚያስችለውን ዕውነት ቢናገሩ ኖሮ እንደ አሳው ገላ የተጠበሰው የሕዝብ ኅሊና ፈጥኖ በሻረና አዲስ የተሃድሶ ሕይወት በዘራም ነበር::



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

በመሠረቱ ሕዝብ ከቅንጅት አጥብቆ የሚፈልገው ፍቅር ነኝ ብሎ እንደጀመረው ሁሉ በፍቅር እንዲጨርሰው እንጅ፣ የሕዝብ ፍቅር ካጡና ከነጡ ጠላቶቹ ያላጣውን ተጠልቶ ማጣላትን አልነበረም:: የፍቅርን መንፈስ አስምሮበት ያወጀው የቅንጅት አመራር ግን በአንድ በኩል ያንን ቃል - ኪዳን አጥፎና በዙሪያው የተሰባሰበውን ኃይል ከፋፍሎ እያናቆረ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ለቅንጅት ጠላቶች መግቢያ የሚሆን በር ወለል አድርጎ ከፍቶ እያስፎከረና የቤቱን መሠረት እያሰቦረቦረ «ችግሩ ቀላል ነው፣ እንፈታዋለን ...ወዘተ» ብሎ መናገር ግን ይሆናል ብሎ ለማመን ቀርቶ ይመስላል ብሎ ለመገመት እንኳ የመሰልነት መሥፈርቶችን የሚያሟላ አይደለም:: ምክንያቱም በእርግጥ እንዳሉት ችግሩ ቀላል ከሆነ እንደችርቻሮ ሸቀጥ ተሸቀዳድሞ አዳባባይ አውጥቶ በማስጣት ለነገር ቸርቻሪ አጫሪዎች ማቅረብና ገበያው እንዲደራላቸው ማድረግ ለምን አስፈለገ የሚል አጠያያቂ ጥያቄ በውስጡ ስላለበት ነው::

ስለዚህ የሚነግሩን ቃላት ሁሉ ኅሊናቸው ሸምቆ ያስቀመጠው የግል ፍላጎት አፈትልኮ እንዳይወጣ የሚደረግ ከበባ እንጅ ከዚህ ደረጃ ላይ የተዳረሰበት ዕውነተኛው ችግር አይደለም የሚል ጥርጣሬ አለኝ:: የማሕበራዊ ኑሮ ገጠመኞችን በየፈርጁ የመግለጽ ተፈጥሮአዊ ታድሎና ተገባራዊ ተመክሮ የነበራቸው አባቶቻችን የሰሞኑን መሰል ድርጊት ሲፈፀም ሲያዩ:

*«አንተም ተው፣ አንተም ተው የሚል ዳኛ ጠፍቶ፣*
*በሬውን ወሰደው ከማነቆው ፈትቶ::»* ብለው ይገልፁት ነበር::

እንዳሉትም ሕግና ሥርዓት ሲጓደል፣ ወይም በዘመነ ወያኔዎች እየሆነ እንዳለው ጨርሶ ሲጠፋ፣ ሀገራዊ ሃላፊነትና ሕዝባዊ ወገናዊነት ደክሞ ሁሉም በየአለበት ዘውድ ቀረሽ አፄ፣ ወይም ማዕረግ የለሽ ፊልድ ማርሻል አድርጎ እራሱን ሲያነግሥ፣ ወይም ራሱን ሲሾም መማማርና መከባበር ቀርቶ መደማመጥ እንኳ ስለሚጠፋ እንደ ዝንጀሮ መንጋ ሁሉም በየመሸገበት ጋራና ጎሬ ሆኖ እያውካካ ወና አድርጎ ከማስቀረትና ውል አልባ ሆኖ ከመቅረት ባለፈ ሌላ ፋይዳ እንደሌለው በዋለባቸው ላይ ውሎ ደጋግሞ የታየ ገሃድ ዕዉነታ ነው::

እኔ እንደሚገባኝ በፖለቲካ ትግል ሂደት አዘውትረው የሚያጋጥሙ ሁለት መሠረታዊ ችግሮች አሉ የሚል ድምዳሜ አለኝ:: የመጀመሪያው ሁሉም እንደፈለገ በመተርጎም የሚጠቀምባቸው ***ሕዝብና ዴሞክራሲ*** የሁሉም ዕምነት ሆነው ሳይሆን ሁሉም አመሉን በጉያው ደብቆ በአንድ ቋንቋ የሚገለገልባቸው መሆናቸው ነው:: ችግሩን የበለጠ አስቸጋሪና ውስብስ የሚያደርገው ደግሞ የበግ ለምድ የለበሱ ተኩላዎችም ከቋንጤዋ ወንበር ላይ ወጥተው ፊጢጥ እስከሚሉ ድረስ እውነተኛ ማንነታቸውን ደብቀው በዴሞክራሲ ስም እየማሉ ከሕዝቡ ጋር አብረው ለመጓዝ መቻላቸው ነው:: ሁለተኛው መሠረታዊ ችግር ደግሞ ከአገር ህልውናና ከሕዝብ ሰብዕና ጋር የተያያዘው ከፍተኛ ጉዳይ ይህን ለማየት ሁለንተናዊ ብቃት (የሞያ፣ የዓላማና የኅሊና ዝግጅት) በሌላቸውና በጠባቡ በሚያስቡ ትንንሽ ሰዎች እጅ እየገባ የሀገር ማፍረሻና የሕዝብ ማጫረሻ መሣሪያ መሆኑ ነው:: ለዚህ አባባሌ በዋቢነት ልጠቅሳቸው የምችል ብዙ መረጃዎች ቢኖሩም ከአእርስቱ ስለሚያስወጣኝ ወደዚያ አላመራም:: በአሁኑ ወቅት በቅንጅት አመራር ዙሪያ በማጎንቆል ላይ ያሉት ለጋ ችግሮች ከዚህ አኳያ የሚታዩና የሚመዘኑ ባይሆኑም ተኮትኩተው የሚያድግበት ዕድል ካገኙ ግን ነገ ወደሚወጋ እሾህነት አይለወጡም ማለት አይቻልም:: ስለዚህ ቅንጅት ከአሁኑ የዴሞክራሲያዊ አሥራር መርሆችን እንዲያከብር፣ በሥርዓት ታርቆ እንዲያድግና መሥመር ይዞ እንዲሄድ ማድረግ ለድርድር የሚቀርብ መሆን የለበትም:: የችግሩን አፈታት በሚመለከት በሁለቱም በኩል ተደጋግሞ ሲነገር የሰማሁት የተስፋ መቆያ አባባል አገር ቤት እንደተመለሱ ሊፈቱት እንደሚችሉ አድርገው ነው:: በእርግጥም እንዳሉት ከሆነ «እሰየ!» የሚያሰኝ ነው:: ነገር ግን አባባላቸውን በጥርጣሬ የማይበት ብዙ ምክንያቶች አሉኝ:-

1. ከጉብኝታቸው ዓላማዎች አንዱ በውጭ አገር የሚኖረውንና የቅንጅት ደጋፊ የሆነውን ኢትዮጵያዊ ኃይል (The Ethiopian Diaspora) በውስጡ



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ያሉበትን ችግሮች በማስወገድ ለማጠናከርና አንድ አድርገው ለማሰለፍ ነበር፡፡ ነገር ግን እንደስንቅ ቋጥረው የወሰዱት ችግር በፊት ከነበረው ችግር ጋር ተዳምሮ ቡድናዊ መከፋፈልን የበለጠ የሚያጠናክር እስከሆነ ድረስ አገር ቤት እስከሚመለሱ መጠበቅ ለምን አስፈለገ?

2. አገር ቤት እንደተመለስን እንፈታዋለን ሲሉ ለእሥራኤሎች በሲናይ በረሃ መናን ያወረደላቸው አምላክ ለእኛም ልቦና ሰጥቶ ኢትዮጵያን ማዳን የምንችልበት ተአምር ይሠራልናል ካልተባለ በስተቀር የተከሰተውን ችግር ፈጥኖ ለማቃለል የሚያስችል ተስፋ ሰጭ አዝማሚያ ስለማታይ፣
3. ችግሩ የተፈጠረው ወደውጭ ሀገር በወጡት የአመራር አባላት መካከል እንጅ አገር ውስጥ ባሉት ባለመሆኑ ሁሉም በየጎኑ ለማሰለፍና ብከላውን እንዲጋሩት ለማድረግ ካልሆነ በስተቀር አገርቤት ያሉት የሚያመጡት ልዩ መፍትሄ ስለማይኖር፣
4. ቅንጅት ነፃ ሆኖ የመንቀሳቀስ ዕድሉ ገና በጥያቄ ምልክት ውስጥ ስለሆነ በተፈጠረው ክፍተት ለመጠቀም የሚፈልጉት ጠላቶቻችን ቸግሩን ለማቃለል የሚችልበት እድል ይሰጡታል ወይ?... ወዘተ ጥያቄዎች በኅሊናየ ስለሚጉላሉ ነው፡፡

ስለሆነም የቅንጅት አመራር አባሎች እነዚህ ሁሉ ታይተዋቸውና ለሕዝብ የገቡት ቃል ኪዳን ከብዷቸው በራሳቸው ላይ ግለ -ሂስ በማካሄድ ሊያስተካክሉት ይችሉ ይሆን? የሚለው ተስፋየ አማራጭ የሌለው መፍትሄ መሆኑ ቢገባኝም የመሆን ዕድሉ ግን በእጅጉ ያነሰ ነው፡፡ ምናልባት እንደተመለሱ የሚወስዱት እርምጃ ቢኖር የምክር ቤቱን አባላት ሰብስበው የጀመሩትን የሳብ ገትር ውዝግብ መቀጠልና እንዳለፈው ጊዜ ከውስጡ ሆነው ቅንጅትን እየወጉ ሲያደሙ እንደነበሩት ዛሬም በአዲስ መልክ እየተኮልኩሉ የቅንጅትን ፍቅር ጨርሶ ለማምረርና ጠንካራ አካሉን እየመለመሉ ለማመንምን ዕድል የሚሰጥ የበለጠ ሰፊ በር ይከፍታል የሚል ከፍተኛ ስጋት አለኝ፡፡ ምክንያቱም ሁሉም የየራሱን ድክመት ሳለመቀበል ሲል ራሱን ንጹህና ቅዱስ አድርጎ በማቅረብ ሌላውን እየኮነነ ውርክቡን ይገፋበታል አንጅ «የወሰዳችሁት እርምጃ ተገቢ ነው» ብሎ አርፎ ሊቀመጥ ስለማይችል ነው፡፡ እንዲህ ያለው ልምድም ጨርሶ የለንም፡፡

ስለሆነም ተቀባይነት አገኘም አላገኘም አማራጭ የሌለው መፍትሄ ነው ብየ በፅኑዕ የማምነበት:-

1. መሠረታዊ ጥያቄው ቅንጅት የመቀጠል ወይም ያለመቀጠል ጉዳይ ብቻም ሳይሆን ከዚያም አልፎ እናት አገር ኢትዮጵያን የማዳን ወይም ጨርሶ የማጣት ጥያቄ ስለሆነ ኢትዮጵያዊ ሐላፊነት የሚሰማቸውና አገርንና ወገንን ማዳን ብቸኛ ዓላማቸው ያደረጉ እንደእነ ፕሮፌሰር ዓለማየሁ ገ/ማርያም የመሳሰሉ አስተሳሰበ ሰፊ ዕውቅ የተግባር ሰዎች ተገናኝተው ያለምንም ይሉኝታ በጉዳዩ እንዲገቡበትና ሁለቱንም አቀራርበው ችግሩን እንዲፈቱ ማድረግ፣
2. «የግል ቁጭትን አገርን በመበቀል መወጣት» በመንፈሳዊ ሕግ ይቅርታ የማያስጥ ሐጢአት፣ በዓለማዊ ሕግ ደግሞ እስከሞት የሚያስቀጣ ከባድ ጥፋት ስለሆነ ግላዊ ስሜትና ፍላጎትን የሙጥኝ ማለትን ትተው የወል ጠቀሜታ ላላቸው እናት ሀገርን የማዳንና ሕዝብን የመታደግ ጉዳይ ቅድሚያና ክብድት በመስጠት ፍቅር ሆኖ ለፍቅር ለቆመውና በሕዝብ ፍቅር ለታቀፈው የቅንጅት ህልውና ሲባል በፍቅር ተሸንፎ እጅ መስጠት ሲቻል፣
3. የብዙ ነገረኞች ነገር የተቋጠረበት ተለጣፊ *ኪስ* ለቅንጅት ኃይል መከፋፈል፣ ለቃል - ኪዳኑ መሸርሸርና ለፍቅሩ መሻከር ዋነኛው ምክንያት ስለሆነ እሱን ገንጥሎ መጣልና በውስጡ የተሰገሰጉትን የሕዝብ ብሩህ ራዕይ አጨላሚ ኩፍኞችንና የወጣቱ ትውልድ ሕይወት ቀሳፊ ኤይድሶችን አራግፎ መድፋት፣
4. ችግሩ ታምቆ ከቆየበት ወጥቶ በይፋ የታወጀውና ተቀጣጥሎ ዓለምን ያዳረሰው በውጭ ሀገር በሚኖረው ኢትዮጵያዊ ኃይል ዘንድ ስለሆነ ይህ ሁለንተናዊ ሙያና ቁሳዊ ጉልበት ያለው ከፍተኛ ኃይል በአንድ ወጥ



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

አደረጃጀት ተደራጅቶ አገር የማዳን ኃላፊነቱን በብቃት እንዲወጣ ከተፈለገ የቅንጅት መሬዎች ወደአገር ቤት ከመመለሳቸው በፊት ችግሩን አስወግደውለት ሊሄዱ ይገባ:: በአጠቃላይ የችግሩ መፍትሄዎች እነዚህ ብቻ ናቸው ባልልም የእነዚህ ተግባራዊ መሆን ግን ጤናማና ጠንካራ የነበረው ቅንጅት በጅምሩ እንዲቀጥል ያስችሉታል ብየ አምናለሁ::

5. ያገር ጉዳይ የሁሉም ከልብ የእኔ ናት የሚሉ ሁሉ ጉዳይ ነው:: የእርሱም/የእርሷም እንዳልሆነች አድርጎ መመልከት ወይም እንስሳት ይመስል መኖአቸው ከተመቸን ሁሉም ሀገራችን ናቸው ባዮች ግን የሁላችንም የሆነችውን እናት ሀገር ለማጥፋት ከዘመቱባት የሁላችንም ጠላቶች ወንጀል የማይተላለፍ ክህደት መሆኑ መታዎቅ አለበት:: ስለሆነም በቅንጅት መሪዎች መካከል የተፈጠረው ለመርዘኞች መርዝ መበተኛ ሆኖ ሊያገለግል የሚችለው ክፍተት ፈጥኖ እንዲገጥምና እንደነበረው እንዲቀጥል ሁሉም በያለበት ዘብ ቁሞ መከላከልና ጤናማ ጩኸት ማስተጋባት አለበት:: በተለይም የቅንጅት ወላጅና ታቅፎ አሳዳጊ የሆነው ሰፊ ሕዝብ በመሪዎቹ ላይ ከፍተኛ ጫናውን ማሳረፍ አለበት::

ሌላው ተደጋግሞ ሲነገር የምሰማው የመሸንገያ አባባል በአንድ የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ የሀሳብ ልዩነት መፈጠር የሚጠበቅ መሆኑን ነው:: በእርግጥ የሰው ልጅ ፍጹምነት ስለሌለው ግላዊ ፍላጎቱን የሚወክል የሀሳብ ልዩነት ወይም የሰፋ ቅራኔ መፈጠር የለበትም ብሎ ለመደምደም አይቻልም:: ፊቱን እያሳየኝ ቀርቶ ድምጹን እንኳን አያሰማኝ እየተባባሉና በቃላት ጦርነት እየተፋለሙ የሀሳብ ልዩነት የሚለው ቀላል ቃል ግን ተመጣጣኝ መግለጫም አይመስለኝም:: ይኸም ሆኖ በአንድ ፓርቲ አመራር ውስጥ የልዩነት መፈጠር የሚጠበቅ ከሆነ ልዩነቱ ከመፈጠሩ በፊት ቅድመ መከላከያው አብሮ ለምን እንዳልታየ ለእኔ ግልጽ አይደለም:: አባቶቻችን *«ጉንዳን ሳይደርስ አስቀድመህ አመድ ነስንስ»* የሚሉትም መሰል ችግሩን በሩቁ ለመከላከል ሲሉ ነው:: አለያማ የጉንዳን ሠራዊት በሩን አልፎ ማጀት ድረስ ከገባ በኋላ በእሳት አስፈራርቶ ለማስወጣት ሲባል የሚደረገው መራወጥ ቤቱን ጭምር እስከማቃጠል የሚያደርስ ጥፋት ያመጣልና ነው::

እኔ እንደሚገባኝ አንድ ችግር አድርሶ የሚሄደው ጉዳትን ብቻ ሳይሆን እንዳይደገም ለማድረግ የሚያስችል ልምድ ጨምር ሰጥቶ ይመስለኛል:: በእኛ ሀገር ግን 17 ዓመት ሙሉ በቅርጻቸው የማይመሳሰሉ፣ በይዘ ቸው ግን አንድ ዓይነት የሆኑ ልዩነቶችን በማስተናገድ የገነባነው ልምድ የሚያረጋግጥልን ቢኖር ቀላሏን ልዩነት እያከበዱና እያወሳሰቡ፣ ጠባቧን ደግሞ እያሰፉና እያራዘሙ በመሄድ መማረርና መበቃቀል እንጅ ችግሮችን በውይይት እየፈቱ ተቻችሎ መኖርና መማማርን አይደለም:: ስለሆነም የዚህ ልምድ አለን ከሚሉት የአመራር አባላት የተከሰተው ችግር የሚጠበቅ መሆኑን ከሚነግሩን ይልቅ ከሚጠብቁት የማይጠበቅ ችግር እንዳይፈጠር ምን ያህል እንደተጠነቀቁና እንደተጠበቡ ገልጸውልን ቢሆን ኖሮ ብእጅጉ ባደነቅናቸው ነበር::

ሌላው ይህን ያልተጠበቀ ክስተት ምክንያት በማድረግ ጎራ በለዩ የብዙሐን መገናኛ ዎች የሚካሄደው የቃላት ጦርነት ነው:: በእርግጥ ድርጊቱ በዙዎቻችን ከአንጀት ያሳዘነና ኅሊናችንን ያቆሰለ በመሆኑ ሆ! ብለን እንድንነሳና አረ - ተው ብለን እንድንጮህ የሚያስገድድ መሆኑን አላጣሁትም:: ይኸም ሆኖ በአንዳንድ የብዙሐን መገናኛዎች አቀራረብ በኩል ጉልህ የሆነ ስህተት መታየቱ የአደባባይ ሚስጥር ነው::

1. የእሣት አደጋ ሠራተኛ ጥሪ ሲቀርብለት ውሃ እንጅ ቤንዚን ጭኖ እንደማይሄድ ሁሉ ከሚገባው በላይ ማራገብ ማንን ጎድቶ አነማንን እንደሚጠቅም ያገናዘቡት አይመስለኝም፣
2. ወልዶ ካሳደገን ጨዋና ታላቅ ሕዝብ የወረስነው ኢትዮጵያዊ ባህልና ጨዋነት እንዲህ ነው እንዴ? የሚያሰኝ ጥያቄ የሚያስከትል ሆኖ መታየቱ፣



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

3. ዕዉነቱን በዕዉነትነቱ ዓይነትና መጠን መገለጽ ሲቻል ስድብና ዘለፋን በዕውነታው ላይ እንደጨው እየነሰነሱ ማቅረብ የበለጠ ያጣፍጠዋል የተባሉ ይመስል በሰፊው ሲጠቀሙበት ተደምጠዋል:: እንዲያውም ከትርፍ ነገር ኪሳራ እንጅ ትርፍ እንደማይገኝ ግንዛቤ ያገኙ አይመስለኝም::
4. በጋራ መድረክ ተቀራርበው ችግሩን እንዲፈቱት ግፊት ከማድረግ ይልቅ በእነርሱ ስብሰባ ላይ አትገኙላቸው ብሎ ማዎጅ ችግሩ እየተባባሰ እንዲሄድ ጊዜና ዕድል መስጠት እንጅ ነገሩ ተፍረጥርጦ እንዲዎጣ ማድረግ አይደለም::
5. እሽቅድምድሙ ለወሬ ጨረታ ወይስ የዜግነትና የሞያ ግዴታን አጣምሮ ለመወጣት የሚደረግ ጥረት? ... ወዘተ በውል ሊታሰብባቸው ይገባል::

ከዚህ ጋር አዛምጀ በአንድ ወቅት ያስተዋልኩትን ትዝብት በትምህርት ሰጭነቱ ብጠቅስ ሊጠቅም ይችላል የሚል ዕመነት አለኝ:: የእንግሊዝ ንግሥት በአንድ ስብሰባ ላይ ማሸለባቸውን ያየ ጋዜጠኛ እሱም ብቻ ሳይሆን እኛ ሁሉ በየምንኖርበት ሀገር ሆነን እስከምናያቸው ድረስ አሰራጭቶት ነበር:: እንደ እኔ አስተያየት እንዲህ ያለው ድርጊት ሥርዓት አልባነት እንጅ የብዙሐን መገናኛዎች ነፃነት ውጤት አይመስለኝም:: ወይስ ሥረዓት አልባነት? ምክንያቱም:-

1. ምንም ይሁኑ ምን ሕዝብ አምኖ ያስቀመጣቸው ንግሥት ናቸው፣
2. ጋዜጠኛው መተቸት የነበረበት ንግሥቲቱ እስከሚተኙ ያስቀመጣቸውን ሕግና ሥርዓት እንጅ ግለሰቧን አልነበረም:: እስከሚያልፋቸው የኖሩ ቀርቶ እስከሚደክማቸው የሠሩ ሰብአዊ ፍጡሮች ሁሉ ቦታና ጊዜ ሳይለዩ እንዲተኙ ይገደዳሉና ነው::

እኛ ግን በኢትዮጵያዊነታችን ከኢትዮጵያዊነታችን ባህልና ጨዋነት ጋር መኖር አለብን ብለን የምናምን ከሆነ በየምንኖርበት ሀገር የቀላወጥናቸውን ሁሉ ከንፁሁ ባህላችን ጋር በማዳቀል እያከሳነውና እያከሰምነው ልንሄድ አይገባም:: መውረስ አለብን ካልን ደግሞ የሚጎዳንን ብቻ ሳይሆን እነሱ ለሀገራቸውና ለብሔራዊ ጥቅማቸው ... ወዘተ. እንዴት ናቸው? ብለን በመጠየቅ የሚጠቅመንንም አብረን መውረስ ይኖርብናል::

በአጠቃላይ ግን ስለብዙሃን መገናኛዎች ወቅታዊ ሥርጭት ሳነሳ ነገሮችና የነገሩ መርዝ ቀማሚዎች ተድበስብሰው ይታለፉ ማለቴ አይደለም:: ያ፣ ሥርዓት ባለው መልኩ ሊቀጥል ይችላል:: ቃላት ሳይመርጡና ደረጃ ሳይበጅለት በጅምላ የሚካሄደው ጠረባ ግን ልባሱን አልፎ አጥንት ድረስ ሠብሮ እየገባ የሚያቆራርጥ እንጅ የሚያቀራርርብ አይመስለኝም:: ምክንያቱም በጦር ከተወጋ ይልቅ በምላስ የተወጋ ቁስል በቀላሉ እንደማይሽር ደህና ሆኖ የሚታዎቅ ይመስለኛል:: ስለሆነም የፕሮፓጋንዳው ሥራ ማተኮር ያለበት መከፋፈል የሚያስከትለውን ጉዳትና ለአንድነት በአንድነት ቆሞ መታገል የሚያስገኘውን ገደብ የለሽ የጋራ ጠቀሜታ በማመላከት ዙሪያ መሆን አለበት እላለሁ:: ይህ ዛሬ እኛ ጎራ ለይተን ትናንት እናሞካሻቸው በነበሩ መሪዎቻችን ላይ የምንወረውረው አጥንትን ሠብሮ የሚገባ ዘለፋ ከቀጠለ መሪዎቹ አንድም በጊዜ ሂደት ስህተታቸው ገብቷቸው አልያም በሀገር ወዳድ ሽማግሌዎችም ተመክረው ስህተታቸውን በማረም ወደ እርቅና አብሮ መሥራት እንዳይመጡ ታላቅ እንቅፋት ይሆናል ብየ እሰጋለሁ::

ከዚህ ጋር ተዛምዶ የሚነሳው ሌላዉ አጣያያቂ ጉዳይ እኛስ የድርሻችንን ለመወጣት ምን እያደረግን ነው የሚለው ነው:: በቅንጅት መሪዎች ላይ አነጣጥረን በገንቢም ሆነ በአፍራሽ ጎኑ ዘመቻ ከቀጠልን ይኸውና ሁለት ወር ሊሞላን ነው:: በሌላው ላይ ለመዝመት የሚያስችል ልምድ ያለን የመሆናችንን ያህል በየራሳችን ድክመት ላይ ለመዝመት ግን ድፈረቱና ቆራጥነቱ ፍፁም የለንም:: ለምን ቢባል አንድም ኅሊናችን ዝግጁ ባለመሆኑ፣ አሊያም ከተጠያቆዎቹ አንዱም እኔ ልሆን እችላለሁ ብለን እራሳችንን ለመጠየቅ አጥብቆ ስለሚከብደን ሊሆን ይችላል:: እኔ እንኳ የጠመንጃው እንጅ የወንጌሉ ባለሙያ ለመሆን ባይዳዳኝም ሮሜ (3)ን ጥልቅ ሚስጥሩንና



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

የአንድምታ ትርጉሙን ለባለሙያዎቹ ትቼ ጥሬ ቃሉን አንብቢያለሁ:: ቃሉም እንዲህ ይላል:-

***«ሰው ሁሉ ኃጢያተኛ ነው፣ አንድ እንኳ ጻድቅ የለም፣ አስተዋይም የለም...»***

አዎ! ማነው ንጹህና ቅዱስ? የጥፋተኝነታችን ዓይነትና መጠን ካላበላለጠን በስተቀር ባለፉት ዓመታት በማዎቅም ይሁን ባለማዎቅ የእናት ሀገሩን ዓይን ለማጨለም የችግር አሻዋ ከመበተን ጀምሮ ህልውናዋን ጨርሶ የሚደፈጥጥ ቋጥኝ እየፈነቀሉ ያላንከባለሉ ቢኖሩ እጅግ በጣም ጥቂት ዕድለኞች ኢትዮጵያውያን ብቻ ናቸው:: ስለሆነም አገር እናድንና ትውልድ እንታደግ ከተባለ መጫጫህና መረባረብ ያለብን በቅንጅት መሪዎች ላይ ብቻም ሳይሆን እኛም ከላይ የጠቀስኩት መንፈሳዊ መልዕክት አጉልቶ በሚያሳየን እኛነት ላይ ቆመን በእኛም ላይ አብረን እየጮህን አብረን ልናድንና አብረን ልንድን ይገባል እላለሁ::

ጽሑፌን የማጠቃልለው ሦስት ነጥቦችን በማሳሰቢያ መልክ አቅርቤ ነው:: የመጀመሪያው የቅንጅትን ስም ለመለወጥ ከሚሰማ አዝማሚያ ጋር ተያይዞ ያደረብኝን ስጋት የሚገልጽ ነው:: እኔ እንደገባኝ ***«ቅንጅት አልተከፈለም፣ ወደፊትም አይከፈልም»*** ሲሉን የነበረውን ኃይልና ጉልበት እንደያዘና ስምና ክብሩን እንደጠበቀ ይመስለኛል:: አላያማ ለራሱ ስምና ክብር ያለቆመ ቅንጅት ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዊነት ይቆማል ብሎ ለማመን ያስቸግራል:: የቅንጅት አመራር ካቀረባቸው ቅድመሁኔታዎች አንዱ የቅንጅትን እውቅና የማገኘት ጥያቄ ይመስለኛል:: ስለዚህ በዚያ ላይ ገትሮ በመያዝ እውቅናውን ማስከበር እንጅ ስለስም ለውጥ አስቀድሞ በር መክፈት ተሸናፊነትን አምኖ እንደመቀበል የሚቆጠር ነው:: ጠላቶቻችን የታሪክ ዕዳ የማይከብዳቸውና የሕዝብ ቀርቶ የእግዚአብሔርን ፍርድ እንኳ የማይፈሩ አረመኔዎች በመሆናቸው ዛሬ በቅንጅት ስም የተጀመረው መራድ ቀጥሎ «ይሄ ብቻ በቂ ስለማይሆን እናንተም ጦርነት ናፋቂ ነፍጠኞች ስለሆናችሁ ስማችሁን ብቻ ሳይሆን ጾታችሁንም ለውጣችሁ ካልመጣችሁ ዕውቅና አንሰጣቸሁም» ቢሉ ምን ሊኮን እንደሚቻል አላውቅም::

በመሠረቱ ቅንጅት በኢትዮጵያ ሕዝብ ደም ውስጥ ሠርፆ ገብቶ የተዋሃደና በሥነ - ልቡናው ተቀርፆ የተቀመጠ የተስፋ ሕይዎቱ መጋቢ ነው:: ስለዚህ ስሙን ለመለወጥ በቅድሚያ ሕዝቡን አፍኖ እስትንፋሱን እንደማሳጣትና ደሙን መጦ በቁሙ እንደማድረቅ ስለሚቆጠር አባል ባልሆንም በድጋፍ ሰጭነቴ በብርቱ እቃወመዋለሁ:: ትግል ሲባል ደግሞ ለዕምነት በጽናት ቁሞ እስከመጨረሻው መፋለም እንጅ እየተልፈሰፈሱ መውደቅ ማለት አይደለም:: ደግሞስ መንፈስ ነው ያለነውን ቅንጅት ሰው አዳኝነቱን አምርረው የጠሉ ጠላቶቹ የእነሱን ግብር እንዲምርስ ፈልገው ሰይጣን ነው ቢሉት እንቀበላለን ማለት ነው?

ሁለተኛው የማሳሰቢያ ነጥቤ "HR2003" ን የሚመለከት ነው:: በቅድሚያ ይህን ሕግ ሀሳቡን ከማፍለቅ ጀምሮ እዚህ ደረጃ ላይ እንዲደርስ ላደረጉት ውድ ኢትዮጵያውያን ወገኖቸ ያለኝ አክብሮትና አድናቆት ከፍተኛ መሆኑን መገለጽ እወዳለሁ:: ወደፊትም ለውጤት እስከሚበቃ ብቻም ሳይሆን የወያኔዎችን እልህ ለማስጨረስና የቃል ኪዳን ጌቶቻቸውን ለማሳፈር ሲባል ጅምራቸውን አጠናክረው እንዲገፉበት በዚህ አጋጣሚ ለማሳሰብ አወዳለሁ::

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ እኛን ነፃ የምናወጣው እኛው ራሳችን በምናካሂደው የተቀናጀ ጥረትና በምንከፍለው ክቡር መስዋዕትነት እንጅ ውሻል ሆና እንድትደግፈን እንደችግር ቀን እህል በመቁኑን ተመጥና በምትቸረን የሞግዚት ሕግ መሆን የለበትም:: እንዲያውም አገራችንና ሕዝቧ በአሁኑ ወቅት ከተጋረጡባቸው ሁለንተናዊ መናጋትና አስከፊ ማህባራዊ ቀውስ ውስጥ የወደቁት እነማን ተባብረው ዘምተውባቸው እንደሆነ ጠንቅቀን የምናውቅ ይመስለኛል:: ስለዚህ ትላንት አደላድሎ የገደለ ጠላት ዛሬ ያድነኛል ብሎ መዘናጋት ታሪክ ደጋግሞ ያረጋገጠውን ኢትዮጵያዊ ሰውነታችንን ጥለን እንደፈለጉ የሚያደርጉን የመገልገያ እቃዎች ሆነን እንዳንገኝ አብረን ልናስብበትና ልናብሰለስለው ይገባል:: ሰዎቹ እንደሆኑ የራሳቸውን ሕግ ቀርቶ የእኛንም ሰብዕና እንደፈለግን ለመተርጎም እንችላለን ብለው የሚመኩ ስለሆኑ ትላንት



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

በውል ያላወቋቸው አባቶቻችን በእነሱ ላይ የሠሩትን ታሪክ ዛሬም እኛ ተከታይ ልጆቻቸው ልናድሰው ይገባል።

ሦስተኛው ማሳሰቢያየ የቅንጅትን መሪዎች በቀጥታ የሚመለከት ነው። የግንቦት 97 ምርጫን ተከትሎ የመጣውን ወያኔ ፈጠር ውዝግብ አቅጣጫ ለማሳትና ትርጉም ላማሳጣት ሲባል በዲፕሎማሲ ሽፋን ይካሄድ የነበረው የመሰንከያ ከበባ ያሳደረብኝን ስጋት ተምርኩዤ በአንድ ወቅት ለቅንጅት መሪዎች የሚከተለውን ተማፅኖ አቅርቤላቸው ነበር፣

*«... የቅንጅት አመራር አባሎች እነዚህን ሁሉ ከእኔ በበለጠ ጠንቅቀው እንደሚያውቋቸው ባውቅም አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የበለጠ ማዎቅ የበለጥ ሊያሳስትና ራስን ሊያስት እንደሚችል በብዙዎች ላይ ውሎ ስለአየሁ የሚያልፍ ችግር የማያልፍ ታላቅ ስማችሁን እንዳይሠብረውና የማይደበዝዝ ታሪካችሁን እንዳያሳድፈው በብዙ በምትጨነቁላት እናት ሀገራችንና ብዙ ችግሮችን በተጋፈጣችሁለት ወገናችሁ ስም እማፀናችኋለሁ።» (ገጽ 16)* የሚል ነበር።

በአሁኑ ወቅት የተከሰተው አሳሳቢ ብቻም ሳይሆን አሳዛኝም የሆነው ድርጊት የሚያሳየን ቢኖር ብዙ የሚያውቁት ታላላቅ ሰዎች ለእነሱ ያልታዩዋቸው ብዙ ስህተቶች መፈፀማቸውንና በቅንጅት ላይ ተስፋውን የጣለውን ሕዝብ ሁለት ጊዜ (ትላንት በመታሠራቸው ዛሬ ደግሞ የተስፋውን ውጋጋን መልሶ የሚያጨልም ችግር በመደቀናቸው) ማሳዘናቸው ነው። ታዲያ ይሄ የሰለጠነ ፖለቲካ እናሰፍናለን ከሚሉ የሰለጠኑ ፖለቲከኞች የሚጠበቅ ነውን? «ምንም ታቦት ቢሆን ሰው መላክ አይሆንም» እንደተባለው ምንም ያህል ትልቅ ሰው ሆነ ወይም በዕውቀት የጠለቀና የመጠቀ ቢባል የሰው ልጅ በተፈጥሮው ፍፁም ባለመሆኑ ይህ ደካማ ጎኑ እየጎተተ ከእምነት ጎዳናው ለማስወጣትና አቅጣጫ ለማሳት በሚያደርግበት ተጽዕኖ ምክንያት የሕዝብን ስሜት ሳይለኩና ፍላጎቱን ሳይከተሉ የራስን ብቸኛ መንገድ ብቻ መርጦ መጓዝ ትላንት እንደታዳጊ መልአክ ተቆጥሮ ሊሰገድለት የተቃረበን ስምና ክብር እንዳልባሌ እቃ አሽቀንጥሮ እንደመጣልና አንኮታኩቶ እንደመሥበር እንዳይቆጠር አጥብቄ እሰጋለሁ።

ይህን በማዘከር ጽሑፌን የማጠቃልለው የቅንጅት መሪዎችን *«ምን እየሠራችሁ ነው?»* የሚል አንድ ቀላል መስሎ የሚታይ ግን ከባድ ጥያቄ ጠይቄ ነው። ማጠናከሪያው ጥያቄ ደግሞ፣ «ቅንጅት በማስመሰል የተካኑት የመሆን ድሃዎች ሲነግዱ የኖሩበትን የማጭበርበሪያ ጭንብል ቀዳዶ በመጣል እርቃናቸውን ያስቀራቸውንና ሠርጅቶ የጣላቸውን አገር አጥፊና ጥቁር ደም አቃቢ የሆኑትን ግብረ - አራዊት ለማንሳት ነው? ወይስ ቅንጅት እንደጀመራቸው እስከመጨረሻው አንኮታኩቶ እንዲጥላቸውና በሁሉም ነገር የመጀመሪያው ሆኖ በመገኘት አዲስ የታሪክ ምዕራፍ እንዲከፍት ለማድረግ ነው? የሚል ነው።

ለእኔ ቀርቶ በሞያው ለተካነው ለአቶ አዲሱ አበበ እንኳ መልስ ያላጡት የፖለቲከ ሰዎች «ቅንጅትን ከገዳዮቹ ለማዳን እንጅ ለመግደል አይደለም» እንደሚሉኝ ደህና አድርጌ አውቃለሁ። እንግዲያው ጽኑዕ ዕመነታችሁ ይህ ከሆነ በቃላችሁና በተግባራቸሁ መካከል መጋጨት ቀርቶ መጣረስ እንኳ እንዳይኖር ይህችን መልዕክት አጢኑልኝ ብየ ጽሑፌን እደመድማለሁ።

እንደሚታወቀው የንስሃ አባቶች ለመንፈሳዊ ሕይዎት ድህነትን፣ ለስጋዊ ፍላጎት በረከትን ያሰጣሉ ተብለው የሚታመንባቸው ናቸው። መምህሬ አልታሰብ የተባሉ ካህን በኑሮአቸው ደከም ያሉ በመሆናቸው ሰበብ አስባብ እየፈለጉ ወደንስሃ ልጆቻቸው ቤት ጎራ በማለት አፋቸውን ሲሸነግሉ ኖረው ከዕለታት አንድ ቀን አይቀሬ ጥሪ ይደርሳቸውና ይሄዳሉ። መምህሬ አልታሰብን በድንብ አድርጎ የሚያውቃቸው የንስሃ ልጃቸው፣

*«ያ መምህሬ አልታሰብ የካህን አውታታ፣*
*አርሱው ታሥሮ ሄደ እንኳን ሰው ሊፈታ።»* ብሎ አስለቀሰላቸው ይባላል።



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

እንግዲህ ሰባ ሚሊዮን ሕዝብ ከወያኔዎች እሥር ቤት ያስፈታሉ ተብለው ከፍተኛ ዕምነት የተጣለባቸው ታላላቅ ሰዎች፣ ከደመኛ ጠላቶቻችን ጋር ያለውን ልዩነት ሳይቀር በእርቀ ሰላም ፈትተን በሀገራችን ውስጥ ዘላቂ ሰላም እናሰፍናለን ብለው የሚያምኑ የቀንጅት መሪዎች የውስጣቸውን ችግር የመፍታት ክህነቱ የለንም ብለው በእንደዚህ ያለው ትዝብትና የታሪክ ተወቀሽነት ላይ እንዳይወድቁ ልንፀልይላቸውና ዙሪያውን ከበን ልንደግፋቸው ይገባል:: እነርሱም የእኛን ጨኸትና ከበባ አቃልለው ቢያዩት እንኳ ታሪክ በክብር ማኅደር የመዘገባቸውንና ተተኪ ትውልድ ሁሉ የማይረሳቸውን በአጥፊዎች ዘመን እንደቁራዎቹ የኢትጵያ ሕዝብ ካነሠሮች ሳይሆኑ የኖህ እርግብ የሆኑንን የክብርት አና ኀሜዝን ትዝብት ሊፈሩ ይገባል እላለሁ:: ስለቅንጅት የመሠከርነውንም ሁሉ ቃል አባዮች መስለን እንዳንታይ ሊያዝኑልን ይገባል::

*የፍቅር አምላክ ፍቅር የነሳንን ልቦና ይስጠን!*
*እጆቿን ወደእሱ ዘርግታ ዘወትር የምትለምነውን እናት አገራችንንም ይታደግልን! አሜን!!*

ጥቅምት 2000 ዓ.ም.



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com